ዴሞክራሲያ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

ዴሞክራሲያ ቅጽ 33 ቁጥር 8 ግንቦት 2000 ዓ.ም.

## ሀገር ለብዙሀን፤ ሙሉ መብት ለግፉዓን

በሀገሩ ኩሩና ባለሙሉ መብት ዜጋ ለመሆን ሲታገል የቆየው ሰርቶ አደሩ ሕዝብ ዛሬም ቢሆን ዓለም የሰራተኞች የምትሆንበትን ቀንና ጊዜ እየጠበቀ መሆኑ በገሀድ የሚታይ ነው:: ሰርቶ አደርነት ከባርነት በስስ ሸማ የተለየ ሆኖ ከመቆየቱ ባሻገር መብቴ ይከበር ያለው ሕዝብ መናፍቅ ተብሎ፤ ክብረ ነክ ተናገረ ተብሎ፤ ፀረ ሰላምና ፀረ አብዮት ተብሎ ተፈርጆና በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ትምክህተኛ ወይም ጠባብ የሚልም ቅፅል ተለጥፎበት ሲወገርና ሲሰቃይ ወይም ሲገደልና ሲሳደድ ብዙ ዓመቶች በሶስት ፀረ ሕዝብ ሥርዓቶች ስር አልፈዋል:: በዓለም የሰራተኞች ቀን በሰላም ተሰልፈው መብቴ ባሉ የተጨፈጨፉትን፤ በአዋሽ አስበተፈሪ፥ ድሬዳዋ፤ ባሕር ዳር አዲስ አበባ የተገደሉትን ከአበራ ጉሙ እስከ ማርቆስ ሀጎስ፤ ከዳሮ ነጋሽ፥ ታደሰና እስከሌሎችም መሪዎች ስንዘክር የኢትዮጵያ ላባደር ለሀገሩና ለመብቱ የሚጠበቅበትን መስዋዕትነት መክፈሉን እንገነዘባለን:: ዛሬ ባይሆን ነገ፤ ነገ ባይሆን ተነገ ወዲያ ዓለም የሰርቶ አደሩ ሕዝብ፤ የብዙሀኑ መሆኗ አይቀሬ ነውና የኢትዮጵያ ሰርቶ አደር ሕዝብም ማለትም ብዙሀኑ ውሎ አድሮ የሀገሩና የመብቱ ባለቤት መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም::

የሀገር ባለቤት ብዙሀኑ ናቸው ስንል በተለምዶ ሕዝበኝነት ቃላትን ለመደርደር ሳይሆን ከመሰረታዊ ሰብዓዊና ፍትሀዊ አቀዋምና እምነት በመነሳት ነው:: ሀገር ለጥቂቶች ገነት ለብዙዎች ገሀነም ሆና መቀጠሏን ልንቀበል አንችልም:: በተለይም የጥቂቶች የእንድልቅ ኑሮ፥ ምቾትና ሀብት በብዙሀኑ መበዝበዝ መበደል፥ መብት አልባና የጭቆና ሰለባ መሆንን በግድ ጠያቂ ከሆነ፤ ህብረተሰቡ ከባድ ችግርና ለውጥን የግድ የሚል፥ ኢፍትሀዊ ሁኔታ ውስጥ እንዳለ ግልፅ ይሆናል:: በአፄው ዘመን የተወሰኑ ገዢዎች፥ ፀሐይ የወጣች ለእኛ ብቻ ነው በሚል ብዙሀኑ ቀንን እንዳያያት፥ እንዳያገኛት ለማድረግ ቆርጠው በመነሳታቸውና አገዛዛቸውም ግፈኛ በመሆኑ፤ ሥርዓቱን አለመታገል ሰብዕናን መካድ ሆኖ ተሰይሞ በመገኘቱ፤ የነቁና ህሊናቸው ያልሞተባቸው ክፍሎች ለትግል ተነስተው ከሰርቶ አደሩ ሕዝብ ጋር አብረው በአብዮት ገረሰሱት:: የሕዝብ የየካቲት አብዮት በታጠቁ ፀረ ሕዝቦች ሲደናቀፍም ለአዲስ ባለነፍጥ በ"ሰላም ገብሮ" መኖር በ"ብልህነት" እና በ"ፈሪ ለእናቱ በረከተ" ተፈርጆ፤ እምቢኝ ለጭቆና ማለት ለሽብር ራስን ማጋለጥ በሆነበት ያኔም ቢሆን ጥቂቶች ብዙሀኑን ረግጠው ሊገዙ ተነስተው ነበርና፤ መራራ ትግል ተካሂዶና ከባድ መስዋዕትነት ተከፍሎ

ከ17 ዓመት በኋላ ያ ፅልመት ተወግዷል፡፡ ብዙሀኑ መሰረታዊ መብትን ካጡ፤ ያም ካደሩ ጥቂቶች ብቻ ከበሉ፤ የእንባቸው ጎርፍ ለጥቂቶች መደሰቻ ከሆነ፤ ጥቂቶች በሚሊዮን ብር ሲጫወቱ ብዙሀኑ ደሞዙ 40 ብር ሆኖ የጤፍ ዋጋ ከደሞዙ አስር ዕጥፍ በላይ ሆኖበት የሚበላው ካጣ፤ የጥጋብ ቁንጣን ለጥቂቱ ገዳይ ረሀቡ ለብዙሀኑ በሆነበት፤ ጥቂቶች በቪላዎችና ዘመናዊ ቤቶች ሲንደላቀቁ ብዙሀኑ መንገድ አዳሪ ከሆነ፤ ጥቂቶች ጉንፋን ያዘን ብለው ወደ ባዕድ ሀገር ለህክምና ሲጓዙ ብዙሃኑ በቀሳፊ በሽታ እንኳን ተይዞ አንዲት እንክብል ኪኒንም ሲያጣ፤ ብዙሃኑ በሀገሩ የዜግነት መብት ሲነፈግና ፍትህ ደብዛዋ ጠፍቶ ግፍና መከራ ሲነግሱ፤ ለብዙሀኑ ያልሆነች ሀገር ለጥቂቶች አትሆንም ብሎ ማመፅ ከግዴታም ባሻገር ሰብዕናን ማስከበር ነው፡፡ ጭቆናን አልቀበልም ብሎ ማመፅ ኢትዮጵያዊነት ነው ስንል ማጋነን ነው ከተባለም መለያችን ሀገርን የብዙሀኑ ለማድረግ ያለ ቆራጥነትና የትግል መንፈስ ሊሆን ይገባዋል፡፡

ያለፈ ታሪክን ፀጋ ለዛሬ ድክመት ማጠየቂያ ለማድረግ መነሳት ስህተት ቢሆንም ታሪክን እንደ መስተዋት መጠቀሙና ሊደገሙ ከሚችሉ ስህተቶችም መራቁ ተገቢ ነው፡፡ በዚህ መንፈስ ያለፈውን ታሪካችንን ስንመለከት ፀጋውንም መርገሙንም፤ ጀግንነቱንም የሚያኮራውንም መገንዘባችን ሊታለፍ የማይችል ግዴታ ነው፡፡ በረጅሙ የታሪክ ሂደት ግን ሰፊው ህዝብ ማለትም ብዙሃኑ ሁሌም ሲጨፈለቅና በመከራው ላይ ቤተመንግስት ሲሰራበት መባጀቱ ሊካድ የማይችል ሀቅ ነው፡፡ ጢሰኛውና ላባደሩ፥ መሬቱና ላቡን የተነጠቀው አርሶ አደር፥ ከአፓርቴይድ የተመሳሰለ ዘረኝነትን ለሚጭኑበት ባዕዳን አሳልፎ የተሰጠው የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ዓይነቱ ላባደር፥ አለምህረት የተበዘበዙት ሴት ላባደሮች፥ የፋሺስቱ ፍጅት ሰለባ የሆኑ ብዙ ሺዎች፥ ስየል ተቀብለውና ተቆርጠው ተቆራርጠው የተገደሉት ማርቆስ ሀጎሶች፥ ኦስማን አሊዎች፤ ሀገሩን የተከለከለው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሞላ የፃፈው ታሪክ የትግልና የጀግንነት እንጂ የባንዳነት ባይሆንም ሀገርና ወገንን ክደው ለሕዝብ ጠላት--ባዕድ ሆነ ሀገር በቀል--ያደሩና ሀገርን ያደሙም አልነበሩም ማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ታሪክ በለስ በቀናው እየተከለሰች ባንዳው የታሪክ ባለቤት ሆኖ ሲነሳ ለሀገር የደማና የሞተው ደግሞ ወደ ጭቃ ሲጣል መታዘብ የታሪካችን ጠባሳ አካል ሆኖ ቆይቷል፡፡ ሆነናም ታሪኩን ያላወቀ ትውልድ ሲመጣ ለአያቱ ገዳይ ይዘፍንለት ገባ፡፡ የታሪክ ክለሳውም መረን የለሽ ሆኖ ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢ፤ አብሮ የኖረው ሕዝብ ባዕድ፤...ወዘተ ተባለና በዚሁ ባዕዳን በደስታ ባስተጋቡት የሀሰት ዘመቻ መሰረት ብዙ ደም ፈሶ የሀገር አንድነትና ህልውናም ለከፋ አደጋ ተጋልጧል፡፡ ብዙሀኑ ታሪክን ወደፊት እየገፋ ቢያስጉዝም ምስጋናው ለገዢዎችና ለእነ እገሌ ተብዬዎች ሆኖ ታሪክ ሰሪው ስሙ ሳይነሳ ክብሩም በተገቢ ደረጃ ሳይሰጠው ይቀራል፤ ቀርቷልም፡፡ ይህ በአፄው ዘመን ቦታ ይዘው ለነበሩ ባንዶች ያመቸ ክስተት ነበር፡፡ ጊዜ ሲያልፍም ያኔ ሕዝብን ያስለቀሰው ሥርዓትና አፄው ዛሬ ሲሞገሱም ለማዳመጥ ተገደናል፡፡ ትላንት ቀይ ሽብር ይፋፋማል ብለው ስንቱን ታጋይ ወጣት የፈጁትም ዛሬ ራሳቸውን ታጋይና ሀገር ወዳድ ብለው ብቅ ማለታቸው ብቻ ሳይሆን ሌላውን ከመድረክ ሊያባርሩ ሲገፋተሩ እያየን ነው፡፡ ትላንት ሀገርን በጋራ ሲገነጣጥሉ የነበሩትም ዛሬ አቅዋማቸውን በሚገባ ሳይቀይሩ ሆነ ላደረሱት ጥፋት ሕዝብን ይቅርታ ሳይጠይቁ

ጀግና በሉን ብለው ሲውገረገሩም እያየን ነው። ታሪኩን የረሳ ስህተቱን ይደግማል፤ በሕዝብ ደረጃ ሲከሰት ሀገርንም ሊያሳጣ መቻሉ ደግሞ አከራካሪ አይደለም።

ከታሪክ ማለትም ሕዝብ በደሙ ከተወልን ቅርስ ተገቢውን ትምህርት እንቅሰም ከተባለ ደግሞ ሕዝብ ከባድ መስዋዕትነትን እየከፈለ ቢገኝም ለወሳኙና መጨረሻ ድሉ አለመብቃቱ ምክንያቱ ሊመረመር ይገባል። በአፄው ዘመን የመሪ ድርጅት አለመኖር--እንዲያውም በዘመናዊ ደረጃ የተደራጀ የፖለቲካ ድርጅት አለመኖሩ--ከሁሉም በላይ ዋናው ድክመት ስለነበረ ለዚህ መፍትሄ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ ኢሕአፓ ሊመሰረት በቃ። ይህ ድርጅት ግን ፈርጠም ብሎ ከመገኘቱ በፊት የሕዝብ አብዮት በየካቲት 66 ፈነዳ። ትግሉን ለማጠናከር ድርጅቱ ታሪክ የመዘገበው አዎንታዊ ሚና ቢጫወትም ሕዝብን መርቶ ለድል ለማብቃት አልቻለም። የሕዝብን ድል የነጠቀውን የምርጥ መኮንኖች ቡድን ወይም ደርግ ተብዬውን በጋራ በጊዜ መዋጋት ሲገባም የመኮንኖቹ ቡድን ሲያደናግር አለምንም ደም ለውጥ ሊያመጣ እንደተነሳና ሕዝብ ባይመርጠውም ለአብዮቱ ራሱን ሞግዚት ብሎ ሾሞ በመቅረብ ሳይውል ሳያድር ግን በንፁህን ደም ተጨማልቆ ቢገኝም የጊዜ እንስጠው ዛር ቢያንስ በተወሰኑ ምሁሮች ላይ ሰፍሮ ለአረመኔው ቡድን ድጋፍ ሰጥትዋል። ተራማጁ ኃይልም በዚህ መልክ ሲከፋፈል በደርጉ ውስጥ ያለው አክራሪና አምባገነናዊ ቡድን ሊጠናከር ችሎ ይህ ነው የማይባል ጉዳት በሕዝብና በሀገሪቷ ከማድረሱ ሌላ በዘመናዊ ባንዳነት የተኮለኮሉትንም ተመልሶ አብዮት ልጆቿን ትበላለች በሚል ፈሊጥ ሰለቀጣቸው። የዚህ በሽብር የታጀበ ሂደትና የተንሰራፋው ፋሺስታዊ አገዛዝ ኢትዮጵያን ምን ያህል እንደጎዳት ደግሞ ቋንጃዋ ተቆርጦ ለወያኔ ፈንጋዮች እንደተሰጠች መገንዘቡ ይበቃል። የወያኔ ለሥልጣን መብቃት ደግሞ ኢትዮጵያን ለከፍተኛ መከራ እንደሚዳርጋት ማስጠንቀቂያ ቢሰጥም፤ ለዚህ ጆሮ መስጠትን ትተው ከመንግስቱ የባሰ አይመጣም በሚል ጭፍን ተስፋ ለሀገር ጠላት ሰለባ የሆኑ ጥቂት አልነበሩም። በአጭሩ ባሳለፍነው የታሪክ ሂደት--ሙሶሊኒ ነፃ ያወጣናል ብለው ወራሪውን ጦር ከደገፉት ጀምሮ--ስለ ጠላት ተገቢውን ግንዛቤ ማጣቱ ወይም ጠላትን እንደ ወዳጅ የማየቱ ስህተት ሕዝብንም ሀገርንም ጎድቷል። ይህ አባዜ እስከቅርብ ጊዜም ቀጥሎ ፀረ ሕዝቡን ወያኔ በተመለከተ የተወሰነ የተቃዋሚ ጎራ መሪዎች ያንፀባረቁት ውዥንብር ሕዝብን ድል ከማስቀማት አንፃር የማይናቅ ሚና ነበረው። ጅቡ ለምዱን አውልቆ ጥርሱን አግጥጦ በላሁህ እያለ ባለበትም አሁንም ከወያኔ አገዛዝ ሰላም ይገኛል ብለው ሕዝብን መካድ የቀጠሉ መኖራቸው እየታየ ነው። መጥፊያው መልሚያው የሚመስለው ሰው መጨረሻው ባያምር ምን ያስገርማል?

ህብረተሰብ ባለውና ባጣ፤ በደላው ጥቂትና በሚበደል ብዙሀን የግድ መከፋፈልና ሁሌም ዋይዋይታና እንባ የብዙሃኑ ዕጣ ይሆናል የሚል መለኮታዊ ብያኔ አለ ብሎ በዝምታ ለመቀበል የሚያስገድደን የለም። ሁሉም ዜጋ በሀገሩ ፊት እኩል ነውና፤ ሁሉም ዜጋ እኩል ዕድል ሊኖረውና ኑሮውንም የማካሄጃ መስክ ሊያገኝ ይገባዋልና፤ ሲወለድ ጀምሮ ማንም ዜጋ ለመከራ ከተዳረገ ከመሰረቱ የተበላሸ ሁኔታ ነግሷል ብንል ትክክል ነው። ኢፍትሀዊ ሁኔታ፥ የብዝበዛ ሥርዓት፥ በደልና መከራ

በብዙሁኑ ተጭኗልና ሀገር ገና የሁላችንም አይደለችም ብሎ የብዙሀኑን ጥቅምና ሰብዕና ለማስከበር ማለትም ሀገርን የሁሉም ዜጋ መኩሪያ ሀገር ለማድረግ ሕዝብ መታገሉ አስፈላጊ ይሆናል። የሰው ልጅ ሰብዕናውን ተቀምቶ፤ ጥቂቶች በጫንቃው ዘፍ ብለው እየቀለዱበት፤ ተዋርዶና ነገ ከዛሬ ይብሳል ብሎ እየባነነ፤ የህይወቱ ዕድሜ በገዢዎቹ ፍላጎት እየተወሰነ፤ ተርቦ፥ ታርዞና ተጨቁኖ የሚኖረው ኑሮ ከንቱ ነውና፤ የሀገሩና የመብቱ ባለቤት ለመሆን ማካሄድ ያለበትን ትግል በማካሄድ ማንቱን ያስረግጣል፤ ራሱን ያስከብራል፤ ኢትዮጵያ የሁላችንም ናት ብቻን ሳይሆን መሆን አለባት መልዕክትን በደሙ ዕፎ ታሪክን ይፅፋል። ሕዝብ ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ ሳይችል አይሰጠውም በሚል ፈሊጥ የተጫነበትን ቀንበር በዝምታ ተሸክሞ፥ 'አቅምን አውቆ መኖር ጥሩ ነው ታላቅ ችሎታ ነው' የሚል የሽንፈትን ዘለሰኛ እያዜመ የባርነት ኑሮውን ከተቀበለ ሰብዕናውንና ክብሩን ራሱ አሳልፎ አንደሰጠ ቢቆጠርበት ተገቢ ነው። ሕዝብ እምቢኝ ብሎ ጭቆናን ለማውደም ሲነሳም የሚያምፀው ውሎ አድሮ ባለድል መሆኑን በማወቅ ቢሆንም ሁሌም አመፁ በአመቺ ሁኔታ የሚካሄድ ነው ማለት አይደለም። ድልን እኔ አያታለሁ ወይም ማየት አለብኝ በሚል ማረጋገጫና ዋስትና ካላገኘሁ አልታገልም ሊልም አይጠበቅም። ጠላቴ ኃያል ነውና፤ በትጥቅ የደረጀ ነውና፤ የሚበገር አይመስልምና አልነካውም፤ አልቋቋመውም፤ አልታገለውም ሊልም አይጠበቅም። ሕዝብ ለሰብዕናውና ለክብሩ፥ ለሀገሩና ለመብቱ በሁሉም ሁኔታና ሁሌም መታገል አለበት። ጨቋኙን ሊፈራ ወይም ከመታገሉ በፊት ከገዢው ሆነ ከባዕድ ፈቃድ ሊጠብቅም አይገባውም። የጣሊያን ጦር ኢትዮጵያን ሲወርና አርበኞች በጦርና ጋሻ፥ በእከደከና ሞዜር ሊከላከሉ ሲነሱ የተሳለቀባቸው ብዙ ነበር። የሙሶሊኒ ኃይል አየበገሬ ነውና ብለውም ቀኝ እጃቸውን አንስተው ለጣሊያን ታማኝነታቸውን የገለጡና ሹመት ጥቅምም ያገኙ መኖራቸው ምስጢር አይደለም። ዛሬም ቢሆን ለትግላችን ፈቃድ ከወደ አሜሪካ ካልተገኘ ባዮችና እጅ ሰጪዎች መኖራቸውን እያየን ነው። ይህ አቅዋም ግን በቁም መሞትንና የባርነትን ኑሮ--ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል እንዲሉ--በፀጋ መቀበልን፤ ከውርደት ጋር ተቃቅፎ መኖርን አመልካች ነው። ይህ ደግሞ ከኢትዮጵያዊነት ጋር የተጣላ ጠባይ ነው ብሎ ለመደምደም መነሳትን ትክክልነት ይሰጠዋል። በአጭሩ ሀገር የብዙሀኑ እንድትሆን ሉዓላዊነቷ ተከብሮ እንድትቀጥል መታገል የዜጋ ግዴታ ነው ማለት ነው። በተለይም ሀገርን ነጋ ጠባ የሚያዋርድ ፀረ ሕዝብ ቡድን ለሥልጣን በቅቶ ክብሯንና መሬቷን ለባዕድ እየቸረቸረ ባለበት ለሀገር ክብር አለመታገል በታሪክ ያስጠይቃል። ከሥልጣን የሚያደርሰውንና በሥልጣን የሚያቆየውን ማንኛውንም የባዕዳን እርዳታ ለመቀበል ምንም ዓይነት ችግር የሌለበት ወያኔ፤ የሕዝብ ውክልና ሳይኖረው የአባይ ውሃን አስመልክቶ ከግብፅ ጋር የተዋዋለውም ውል ይዘቱ እስከዛሬ ምስጢር ሁኖ መያዙ ይታወቃል። በቅርቡ የክህደት ሰነድ ከሱዳን ባለሥልጣናት ጋር ለመፈራረም ቃል መግባቱና መስማማቱ የተጋለጠበት ይህ የጥፋት መልዕክተኛ የሆነ ቡድን ካሁን በፊት የሰራው መጥፎ ግብሩና ጉዳቱ አልበቃ ብሎት በቅርቡ የሀገራችንን መሬት ለሱዳን አሳልፎ መስጠቱን እያየን ነው። በአካባቢውም እየደረሰ ላለው የሕይወትና የንብረት መውደምም ደንታ

እንደሌለው አሳይቷል። ይህን ሁሉ ስናይ እኛም የድንበራችንን አጥር ማስከበር ተስኖን የቤት በራችን አጥር እንዲሆን እየጠበቅን ይመስላል።

ሀገራችን ዛሬ ያለችበትን አደገኛ ሁኔታ ስናይ ሁሉም ጨለማ፣ ሁሌ/ም ሁሉም ትግል ሽንፈት ነበር ብሎ መደምደም ከሀቅ መጣላት ይሆናል። የተከፈለው መስዋዕትነት ሁሉ ዋጋ ኖሮት ታሪክን ወደፊት እየገፋ ለሀገራችንም ጠቅሟል። ያ ሁሉ ደም በከንቱ አልፈሰሰም። ያ ሁሉ ወጣት ከታሪክ የተጣሉ ክፍሎች እንደሚሉት ተማግዶ ውጤት አልባ አልሆነም። ዛሬ ተለምደውና አሉ ተብለው የሚወሰዱ ግኝቶችና ሁኔታዎች ትላንት የተደረጉ ትግሎች ውጤቶች ናቸው። ህብረተሰባችን ባለበት ሲረግጥ ምዕተ ዓመት አላለፈም። እንደድሮው ቀጥቅጠው ሊገዙን፣ ወደ ኋላ ሊጎትቱ የሚጥሩት አምባገነኖች ዛሬ መደላደል አቅቷቸው በቀውስ መናጣቸውና ሕዝብንም ሊያደናግሩ አለመቻላቸው የዚሁ ማረጋገጫ ነው። አምባገነኖች በበጎና በራሳቸው ፈቃድ ወሰድናቸው የሚሏቸው እርምጃዎች ውስንም ቢሆኑ የሕዝብ ትግል ያስገኛቸው ድሎችና ውጤቶች መሆናቸው አያከራክርም። ባለፈው ላይ ተመስርቶ ከወሳኙ ድል መድረስን በተመለከተ ግን ዛሬም--በተለይ መሪ ድርጅቶች ነን በሚሉት በኩል--ያሉት ብዥታዎችና ድክምቶች ግን የሚካዱ አይደሉም። ተማርን አወቅን ቢሉም ከራሳችን ሕዝባዊ ትግል ተመክሮ አሰፍላጊውን ግንዛቤ ለመያዝ ያቃታቸው መኖራቸውና ስህተትን እየደገሙና በጮሌ ገዢዎች እየተደናገሩ--አልፎም እየተገዙ--ትግሉን የሚጎዱ መኖራቸው ሀቅ ነው። ይህን ሀቅ መቀበሉ ደግሞ ድክመቱን ለማስወገድና ለዚህ በሽታም መፍትሄ ለመፈለጉ በር ይከፍታል። ሀገርና መብት የብዙሀኑ እስኪሆኑ መታገል ግዴታ መሆኑን ዛሬም ነገም  በመቀበልና በማስረገጥ ለድል ትግሉ መፋፋም አለበት።  ታጋዮች  የገበሩት ደም ፍትህን እየጠየቀ ከመጮህ ባሻገርም ለሀገር የፈሰሰ እንጂ ከንቱ አልቀረምና ዛሬም ያ ደም ባስገኘው ውጤት ላይ ቀሪውን ለማሟላት ትግላችን መቀጠሉ ግዴታ ነው።

ሰው ማለት ሰው የሚሆን ሰው የጠፋ ዕለት እንደተባለው ሁሉ፣ ጀግና የሚባለው ፍርሀት ነግሶ ደፋር በጠፋበት ጊዜ የሚደፍረው እንጂ በድል አጥቢያማ አርበኛ ነኝ ባዩ አደባባይ ይጠበዋል። ታውቆ ፀሐይ የሞቀውን መናገሩ ነቢይ አያሰኝምና ከትግል አንፃር ድል ቀርባ በማትታይባትም ጠረኗን ከሩቁ አሽተውና በሕዝብ አቸናፊነት አምነው ለትግል የሚነሱት የድል ነቢዮች ለሀገር ሉዓላዊነት ሁሌም አስተማማኝ ዘብ በመሆን የትላንት ወዲያ አርበኞችን፣ የትላንት ታጋዮችን እናቸንፋለን መልዕክት ያስተላልፋሉ። አምባገነን ሥርዓቶች÷ ባዕድ ወራሪዎች ሁሉ መቸም ሽንፈት የሚነካቸው ሳይመስሉ በሥልጣን በማን አለብኝነት ተኩራርተው ስለሚወራጩ እውነትም ኃያል መስለው ሊያደናግሩ ይችላሉ። በዘመነ ደርግም ዛሬም በሥልጣን ባሉት ፀረ ህዝቦች ዘንድ የምናየው ቢሆንም ታሪክ ደግሞ አንበገርም ያሉ አምባገነኖች ከትቢያ መቀላቀላቸውን ታስተምራለች። ይህንን የታሪክ መልዕክት ተገንዝበው፣ ግለኝነትን ተቋቁመው፣ ፍርሀታቸውን አሸንፈው ለባለነፍጡ አንሰግድም አንንነብስም ብለው ትግሉን የሚቀጥሉና ለሀገር ለወገን መከራን የሚቀበሉ ሲከበሩ ለገዢዎች በሰበብ አስባቡ የሚሰግዱ ግን በባንዳነትና ማፈሪያነት ተፈርጅው በትውልድም በታሪክም ይወገዛሉ።

ሕዝብ ላይ የተጫኑት ሥርዓቶች ለባንዳ ድልዳል ሆነውና ሹመት ሰጥተው ቢገኙም፤ አንዳንዶች ለሶሰት የተቃረኑ ግን በፀረ ሕዝብነታቸው አንድ ለሆኑ በአማካሪነት አገልግለው ቢከብሩም፤ ለሀገር መሰዋቱና ለሀገር መታገሉ በአፈ ጮሌዎች በሞኝነት ተፈርጆ ያታገለ ድርጅትንም በአስጨራሽነት ማውገዙ ቢደመጥም፤ ሀቅ ብትቀጥንም አትበጠስምና፤ ታሪክ በረጅሙ ሂደት ሀቅን አስፍራ ማለፏ የታወቀም ነውና፤ ሀገርና ሕዝብ ጀግኖችን ሲያከብሩ ከሀዲዎችን፥ ሕዝብ በሰቆቃ ሲጮህ ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው ከገዳይ ጋር የጨፈሩትንና የምን አገባን ግለኞችን ሁሉ የማይጠፋ ውግዘት ያትሙባቸዋል።

በመሆኑም ከሆድ ባሻገር ዓይንን አማትሮ፤ ከግል ስግብግብና ውሱን ጥቅም በላይ የሀገርን ክቡርነት ሚዛን ሰጥቶ፤ ሕዝብን ደም እያቃቡ የሥልጣን ዕድሜውን ሊያራዝም የተነሳውን አገዛዝ በቁርጠኝነት ተቃውሞ፤ ያ የጠፋ ሰላምና ዴሞክራሲን በትግል ነፍስ ልንዘራበት እንችል ዘንድ ዛሬም አንጀታችንን በድግ ጠፍረን መዝመት መታገል ይጠበቅብናል። ኢትዮጵያ ዛሬ ሀገር ሆና የመቀጠልና ያለመቀጠል ጥያቄ አፍጦ መጥቶባታል። እንደተለመደው ደግሞ ረሀብ፤ ቸነፈር፤ ሀዘንና ሰቆቃ ኢትዮጵያን ሰፍረውባት የቆዩ ቢሆንም ፀረ ሕዝቡ አገዛዝ በሀገሪቷ ህልውና ላይ የመጣ ልዩ መዓት በመሆን ያነጠፈላት የከረፋ የድቀት ወለል የክፍፍል ተባዮች የሞላባት ሆኖ ይገኛል። እስቲ እንየው፤ ያልፋል የሚባል በራሱ ጊዜውን ጠብቆ የሚመጣው ህልፈቱ ሀገራችንንም ይዞ ወይም ሰነጣጥቆና ለሶማሊያዊ ውድመት ዳርጎ የሚያከትም ሊሆን ስለሚችል በትዕግስት የሚጠበቅ አይደለም። ባለፉት አስራ ሰባት ዓመታት የወያኔ አገዛዝ የጥቂቶች ብቻ መሆኑን፤ ጎጠኛና በጠባብነት የተቃኘ፤ ምንም ሀገራዊ ስሜት የሌለው መሆኑን፤ ይችን ኩሩ ሀገር ሊያጠፋ የመጣ የዘመናዊ ደርቡሾችና ካራቢኔሪዎች አጋር መሆኑን በሚገባ አስመስክሯል። ኢትዮጵያ የብዙሀኗ ዜጎች ሀገር እንዳትሆን በብሄረሰብ ልዩነት፤ በመደብ ጭቆና፤ ሀገር ወዳዱን በመጨፍጨፍ፤ ሕዝብን እያስለቀሰና እያዳማ በመከፋፈል የወያኔ አገዛዝ ጋሬጣ ሆኗል። በአሁኑ ጊዜ ይህ የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያና የሕዝቧ ዋነኛ ጠላት መሆኑን ከነገረ ቀደም ሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋ ሊረዳው የሚገባ ሀቅ ነው። ኢትዮጵያ ለወያኔና ቅጥረኞቹ መፈንጫያና መደሰቻ ለሕዝቧ ግን ወህኒ ቤትና የስቃይ የመከራ መሬት ስትሆን በዝምታ ወይም በቸልታ ልናይ አንችልም። የማን ቤት ጠፍቶ የማን ሊበጅ ማለት ግዴታ ሆኖ ይገኛል። ይህን ሀቅ በመካድ የሕዝብን ጠላት ወዳጅ ብለው እጅ እጅ ያለውን ትጥቅ አስፈቺ ልፈፋ ከቁም ነገር ወግ ውስጥ ዘንቀው የሚያቀርቡትን ጆሮ መስጠቱ በሀገር ላይ መቀለድ ነው። ከዚህ ቀደም በዚሁ ልሳን ተቀምጦ እንደነበረው ኢትዮጵያን ከሲዖል ወደ ገሀነም የሚወያርዳትን ጎዳና በተመለከተ "ራሱን ጎዳናውን መለወጥ እንጂ መሪዎቹን ብቻ መለዋወጡ ከተባለው ምድረ ፍዳ ገስግሶ ወይም ጥቂት ዝግ ብሎ በመድረስ ደረጃ ለውጥ ያመጣ እንደሆነ እንጂ ሌላ ፋይዳ አይኖረውም--ጽድቅ ሳለ ወደ ኩነኔ እንዳንሄድ" ነበር ያልነው። ዛሬ በመላ ኢትዮጵያ እየተስተጋባ ያለው የትግል ነጋሪትም አቅጣጫውን ስቶ የሀገራችንን ውድቀት በሚመኙ መዳፍ ስር እንዳይገባ፤ ወይም የወያኔ ቡድን በዘረጋልን የእርሰ በርስ ዕልቂት ወጥመድ ተተብትቦ ሀገርን እንዳይጎዳ መከላከል የዜጋ ሁሉ ግዴታ ነው። ወያኔ/ኢሕአዴግ ስልቻ ቀልቀሎ ነውና የወያኔ ምርጫ

**ሁሌም ባልትና ፀረ ሕዝብ ተረት ሆኖ ቀርቷልና ስርየትን ከአውሬዎቹ መናኸሪያ ቤተ-መንግሥት መጠበቁ ሀገር ጎጂ ሞኝነት ነው:: አውቀው የሚጃጃሉና ቅጥረኝነትን በየዋህነት ሽፋን የሚያቀነቅኑ መኖራቸው ባይሳተንም ደግመው ደጋግመው የሚታለሉ ደግሞ ለማይሞኙት ልጓሙን ማስረከብ ይኖርባቸዋል:: የጥፋት ዝናም አከተመ፤ ብረት ወድሮ ገብር የሚልህ ሁሉ ተነነ ለማለት ገና አልታደለምና፤ በሀገርም ውስጥ ሆነ በባዕድ ሀገር የተቃወመን አንገት የሚያርድ አገዛዝ ነውና፤ በላያችን የተሰየመው በእንብርክና በምለላ የዲያብሎስን ልብ ለማራራት ከቶም ሊታሰብ አይገባውም::**

**ሀገራችን ለብዙሀኑ ካልሆነች ለጥቂቶች መፈንጪያ ልትሆን ዘንድ እሺ አንልም:: የብዙሃኑ መብት እስካልተከበረ ድርሰ የማመፅ መብታችንንም ለማንም አሳልፈን መስጠትና በጨንገር እንደሚነዱት ከብት ልንሆን አንችልም:: ሰብዕናችን÷ ኢትዮጵያዊነታችን÷ ታሪካችን አይፈቅድልንም:: ከብዙሀኑ ጋር ሆነን የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ ትግላችንን የምናፋፍመውም ለዚህ ነው::**

**ድል የሕዝብ ነው!!**
**የወያኔ አገዛዝ በሕዝብ ትግል ይወድማል!!**